ምክንያተ ፡ ጽሒፎቱ ፡ ለጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ዳግመ ።

እስመ ፡ ሰብአ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ሶበ ፡ ሰምዕዎ ለሐዋርያ ፡ በመልእክቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ እንዘ ፡ ይብል ንሕነ ፡ ሕያዋን ፡ እለ ፡ ንተርፍ ፡ አመ ፡ ምጽአተ እግዚእነ ፡ ይመሥጡነ ፡ በደመና ፡ ከመ ፡ ንትቀበሎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ውስተ ፡ አየር ፡ መሰሎሙ ፡ ከመ ይከውን ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ በዘመኑ ፡ ለዝንቱ ፡ ሐዋርያ ።

ወአጠየቆሙ ፡ ከመ ፡ ኢይከውን ፡ እሜሃ ፡ ዘእንበለ ፡ ይቅድምዎ ፡ ትእምርታት ፡ እለ ፡ ይከውኑ ፡ በእስተርእዮቱ ፡ ለሐሳዊ ፡ መሢሕ ።

ወይቤሎሙ ፡ ንነግረክሙ ፡ አኃዊነ ፡ በእንተ ምጽአት ፡

ወእንትሙሂ ፡ ውስተ ፡ ማኅበሩ ፡ ዑቁ ፡ ኢያደንግፁክሙ ፡ ፍጡነ ።

ኢትትሀወኩ ፡ እምአእምሮ ፡ ኢበመንፈስ፡ ወኢበነገር ፡ ወኢበመጽሐፍ ፡ ከመ ፡ ዘእምኀቤነ፡ ለእመ ፡ ትመጽእ ፡ ዕለተ ፡ እግዚእነ ፡ አልቦ፡ ዘያስሕቶክሙ ፡ ወኢበምንትኒ ።

ወጸሐፈ ፡ ዘንተ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በሎዶቅያ ወነደጎ ፡ ህየ ፡ ወኢፈነዎ ፡ እሜሃ ፡ ኀበ ፡ ተሰሎንቄ

ወባሕቱ ፡ አጠየቀ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ መቁሕ ፡ በሮሜ ፡ አመ ፡ ፈነወ ፡ መልእክተ ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ቈላስይስ ፡ በብሂሎቱ ፡ ወአንቢበክሙ ፡ ዘንተ ፡ መጽሐፈ ፡ ፈንውዋ ፡ ሎዶቅያ ፡ ያንብብዋ በቤተ ፡ ክርስቲያን ።

ወካዕበ ፡ አንትሙ ፡ ንሥኡ ፡ መጽሐፈ ፡ እንተ ጸሐፍኩ ፡ እምሎዶቅያ ፡ ወአንቢብክሙ ፡ ፈንውዋ ተሰሎንቄ ።

ወአዘዞ ፡ ለጢኪቆስ ፡ ረድኡ ፡ ከመ ፡ ያብጽሕ ዘንተ ፡ መልእክተ ፡ ለሰብአ ፡ ተሰሎንቄ ።

ጳውሎስ ፡ ለተሰሎንቄ ፡ ኹለተኛ ፡ የጻፈበት ምክንያት ።

የተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ፡ በመጀመሪያው፡ ከታቡ፡ ሕያዋን ፡ ኾነን ፡ የምንኖር እኛ ፡ ጌታችን ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በልዕልና ፡ እንቀበለው ፡ ዘንድ ፡ በደመና ፡ ነጥቀው ፡ ይወስዱናል፡ ሲል ፡ ቢሰሙት ፡ ምጽአቱ ፡ በሱ ፡ ጊዜ ፡ ይደረጋል መስሏቸው ፡ ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ሐሳዌ ፡ መሢሕ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረጉት ምልክቶች ፡ አስቀድመው ፡ ሳይደረጉ ፡ ምጽአት፡ እንዳይደረግ ፡ ሲያስረዳ ፡ ጻፈላቸው ።

ወንድሞቻችን ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መምጣት ፡ ገና ፡ እንደኾነ ፡ እንነግራችኋለን ።

ባንድነቱ ፡ ያላችሁ ፡ እናንተ ፡ ምጽአት ፡ ፈጥኖ ፡ ይደረጋል ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ እንዳያሸብሯችሁ ፡ ዕወቁ ።

(ኢበመንፈስ ፡) በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገለጠልኝ ፡ ብለው ፡ (ወኢበነገር ፡) ከሐዋርያት ፡ ቃል ሰማን ፡ ብለው ፡ (ወኢበመጽሐፍ ፡ ከመ ፡ ዘእምኀቤነ ፡) ከኛ ፡ መጽሐፍ ፡ እንዳገኙት ፡ አድርገው ምጽአት ፡ ፈጥኖ ፡ ይደረጋል ፡ ቢሏችሁ ፡ ምጽአት ገና ፡ እንደኾነ ፡ ከማወቅ ፡ ወጥታችሁ ፡ እንዳትታወኩ ፡ በምንም ፡ በምን ፡ የሚያስታችሁ ፡ አይኑር አይለ ፡ ጻፈላቸው ።

ይህን ፡ ከታብ ፡ በሎዶቅያ ፡ ሳለ ፡ ጽፎ ፡ ከዚያው ፡ አኖረው ፡ እንጂ ፡ ያንጊዜ ፡ ወደተሰሎንቄ፡ አላከውም ፡

ያንጊዜ ፡ አስመላኩንም ፡ በሮም ፡ ታስሮ ፡ ሳለ ፡ ለቈላስይስ ፡ ሰዎች ፡ ከታብ ፡ በላከ ፡ ጊዜ ፡

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ተመልክታችሁ በጉባኤ ፡ ያነበቡት ፡ ዘንድ ፡ ወደሎዶቅያ ፡ ላኩት ፡

እናንተም ፡ የጻፍኩትን ፡ መጽሐፍ ፡ ከሎዶቅያ ፡ ወስዳችሁ ፡ ተመልክታችሁ ፡ ወደ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ላኩት ፡ በማለቱ ፡ አስረዳ ።

ይህን ፡ ከታብ ፡ ለተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ፡ ያደርስ ፡ ዘንድ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ጢኪቆስን ፡ አዘዘው ።

www.ethiopianorthodox.org

ቀዳማዊ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ካልእት ፡ አለ ፡ ንሕነ ፡ ሕያዋን ፡ እለ ፡ ንተርፍ ፡ አመ ፡ ምጽአተ ፡ እግዚእነ፡ ኢንበጽሖሙ ፡ ለምውታን፡ (፩፡ተሰ፡ ፬ ፡ ፲፭)፡ ሲል ፡ ሰምተው ፡ ምጽአት ፡ በጳውሎስ ፡ ጊዜ ፡ ይደረጋል ፡ ብለ ዋል ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ገና ፡ እንደኾነ ፡ ስመንገር ፡ ይጽፋል ፡ ንነግረክሙ ፡ አኃዊነ ፡ በእንተ ፡ ምጽአተ ፡ እግ ዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወእንትሙሂ ፡ ውስተ ፡ ማኅበሩ ፡ ዑቁ ፡ ኢያደንግፀክሙ ፡ ፍጡነ ፡ ወኢትትሐ ወኩ ፡ እምእእምሮ ፡ ኢበመንፈስ ፡ ወኢበነገር ፡ ወኢበመጽሐፍ ፡(ም ፡ ፪ ቍ፡፩)ኢትዘክሩኑ ፡ ከመ ፡ እመ ፡ሀሎኩ ኀቤክሙ ፡ አቅደምኩ ፡ ወነገርኩክሙ ፡ ዘንተ ፡ ቍ ፭ ወይእዜኒ ፡ አኃዊነ ፡ ቁሙ ፡ ወዕቀቡ ፡ ትእዛዘ ፡ ዘመሐ ሩክሙ ፡ ወሠርዑክሙ ፡ ዘበቃልነ ፡ ወዘበመጽሐፍነ ፡ ቍ ፲፭ ዘኢይፈቅድ ፡ ይትቀነይ ፡ ኢይሴሰይ ፡ ፫፡፲፩፡ ወለእመቦ ፡ ዘኢይትኤዘዝ ፡ ለቃልክሙ ፡ ወለመጽሐፍክሙ ፡ ይትፈለዋ ፡ ወኢትትሐወልዎ ፡ ከመ ፡ ይትኀፈር ፡ ወከመስ ፡ ጸላኤ፡ኢትረስይዎ ፡ አላ ፡ ገሥጽዎ ፡ ከመ ፡ እኁክሙ ፡ ፫ ፡ ፲፬ ፡ ወዝንቱ ፡ ትምህርትየ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ፡ መጻሕፍትየ ፡ ከመዝ ፡ እጽሕፍ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ይላል ፡ ፲፰ ፡ የጻፈበት ፡ ሀገር ፡ ሎዶቅያ ፡ ክታብ ፡ ወሳጅ ፡ ጢኪቆስ

---

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ ፡ እምጳውሎስ ፡ ወስልዋኖስ ፡ ወጢሞቴዎስ ።

ከኔ ፡ ከጳውሎስና ፡ ከስልዋኖስ ፡ ከጢሞቴዎስም ፡ የተላከ ፡ ክታብ ።

ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘተሰሎንቄ ፡ ምእመናን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ።

በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ አምነው ፡ በተሰሎንቄ ፡ ላሉ ፡ ምእመናን ፡ ትድረስ።

፪ ፡ ሰላም ፡ ለክሙ ።

ቸር ፡ አላችሁን ።

ወጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።(፩ቆሮ ፡፩፡፫ ቈላ፡ ፩፡፪ ፡)

የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋው ፡ ይደፍባችሁ፡ ይደረግላችሁ ።

፫ ፡ ርቱዕ ፡ ናእኵቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ በእንቲአክሙ ፡ አኃዊነ ።

ስለናንተ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ኹልጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ልናመስግነው ፡ ይገባል ።

በከመ ፡ ይደልዎ ።

ለሱ ፡ እንደሚገባው ፡ ባንድነቱ ፡ ምንታዌ ፡ በሦስትነቱ ፡ ርባዔ ፡ ሳንቀላቅል ። አንድም ፡ ሰውን ፡ ጻድቅ ፡ ቢሉት ፡ ሐሰት ፡ ባዕል ፡ ቢሉት ፡ ንዴት ፡ኃያል ፡ ቢሉት ፡ ድካም ፡ ይስማማዋል፡እርሱ ፡ ግን፡ ባዕል ዘአልቦ ፡ ንዴት ፡ ኃያል ፡ ዘአልቦ ፡ ድካም ፡ ጻድቅ ፡ ዘአልቦ ፡ ሐሰት ፡ ነውና ።

አንድም ፡ ለሰው ፡ ማመስገን ፡ እንደሚገባው ። ሰውና ፡ መላእክትን፡ መፍጠሩ፡ ሊያመሰግኑት ፡ ነውና ወበእንተዝ ፡ ፈጠሮ ፡ ለሰብእ ፡ ከመ ፡ ይትለአኮ ፡ በአምሳለ ፡ መላእክት ፡ እንዲል ፡ (ሃይ ፡ አበ አትና)።

እስመ ፡ ዐብየት ፡ ሃይማኖትክሙ ፡ ወፈድፈደት ፡ ተፋቅሮትክሙ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ቢጽክሙ ።(ም ፡፪ ፡፲፫ ፡፩ ተሰ ፡ ፩ ፡፪ ፡)

በሃይማኖት ፡ ከመስሏችሁ ፡ ከወንድሞቻችሁ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ፍቅራችሁ ፡ በዝታለች ፡ ሃይማኖታችሁ ጸንታለችና ።

፬ ፡ ከመ ፡ ንሕነኒ ፡ ንትመካሕ ፡ ብክሙ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለእግዚአብሔር ።

በምእመናን ፡ ፊት ፡ እንመካባችሁ ፡ ዘንድ ፡ እስከንመካባችሁ ፡ ድረስ ፡ ደርሰን ።

በእንተ ፡ ሃይማኖትክሙ ፡ ወትዕግሥትክሙ ፡ በሕማምክሙ ፡ ወምንዳቤክሙ፡ ዘትትዔገሡ ፡ ወትትዌከፉ ።

(፪ ቆሮ ፡፯ ፡፲፬)፡ ስለሃይማኖታችሁ ፡ ታግሣችሁ ፡ ስለምትቀበሉት ፡ መከራ ፡ ጸዋትወ ፡ መከራ ፡ ሃይ ማኖታችሁ ፡ጸንታለች ፡ ፍቅራችሁ ፡ በዝታለችና ፡ ርቱዕ ፡ ናእኵቶ ።

፭ ፡ ከመ ፡ ታርእዩ ፡ ኵነኔ ፡ ጽድቁ ፡ ለእግዚአብሔር ። (ፊልጵ ፡፩ ፡፳፰ ፡)

የእግዚአብሔርን ፡ እውነተኛ ፡ ፍርዱን ፡ ትገልጹ ፡ ዘንድ ፡ እስከትገልጹ ፡ ዘትትዔገሡ ፡ ወትትዌከፉ

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ ይከፍልክሙ ፡ መንግሥቶ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ ተሐምሙ ።(ሉቃ ፡፳፩ ፡፴፯ ፡)
እግዚአብሔር ፡ ስለሱ ፡ መከራ ፡ የምትቀበሉላት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ያወርሳችሁ ፡ ዘንድ ። እን
ድም ፡ መከራ ፡ ለምትቀበሉላት ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ያበቃችሁ ፡ ዘንድ ፡ ታርእዩ ፡ ኵነኔ ፡ ጽድቁ፡
ላለው ።

፮ ፡ ወርቱዕሰ ፡ ይትፌደዩ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕማመ ፡ እለ ፡ የሐምሙክሙ ።(ራእ ፡ዮሐ ፡፲፰ ፡፮ ፡፯ ፡)
(ይትፌደዩ ፡ ሕማመ ፡ እለ ፡ የሐምሙክሙ ፡ ሕማመ ፡) አገባብስ ፡መከራ ፡ የሚያጸኑባችሁ ፡ ሰዎች፡
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ፍዳቸውን ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ ስለአሳቸው ፡ እናመሰግናቸው ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፯ ፡ ወለክሙ ፡ ለእለ ፡ ተሐምሙ ፡ ዕረፍት ፡ ምስሌነ ።
(ተሐምሙ ፡ ምስሌነ ፡ ዕረፍት ፡ ምስሌነ ፡) ከኛ ፡ ጋራ ፡ እንደኛ ፡ መከራ ፡ ለምትቀበሉ ፡ ለናንተ ፡ ግን
ዕረፍት ፡ ስለአሳችሁ ፡ ልናመሰግነው ፡ ይገባል ።
በምጽአቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እምሰማያት ፡ ምስለ ፡ መላእክተ ፡ ኃይሉ ።(ማቴ ፡፳፭ ፡፴፩ ፡)
ከሃሊነቱ ፡ የሚገለጥባቸው ፡ መላእክትን ፡ አስከትሎ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ይትፌደዩ ። እንድም ፡ ዕረፍት
ምስሌነ ።

፰ ፡ ከመ ፡ ይትበቀሎሙ ፡ በነደ ፡ እሳት ፡ ለእ ለ፡ ኢያአምርዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወእለ፡ ኢይሰምዑ ፡ ትምህርተ
ወንጌሉ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ።(ሮሜ ፪፡፰)
ወንጌልን ፡ በማይቀበሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማያውቁ ፡ ሰዎች ፡ ነደ ፡ እሳትን ፡ ይፈርድባቸው ፡
ዘንድ ፡ እንድም ፡ በምጽአቱ ፡ ይትቀበሎሙ ፡ ወንጌልን ፡ የማይቀበሉትን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማያው
ቁትን ፡ ሰዎች ፡ ነደ ፡ እሳት ፡ በመኾን ፡ በነደ ፡ እሳትነት ፡ ይገጥማቸው ፡ ዘንድ ፡ ይመጽእ ።

፱ ፡ ወይረክቡ ፡ ፍዳሆሙ ፡ ኩነኔ ፡ ኃጕል ።
ኃጕለ ፡ ኩነኔ ፡ ቢል ፡ ይቀናል ፡ ፍዳቸውንም ፡ ፈርዶ ፡ የሚያመጣባቸውን ፡ ጥፋት ፡ ይቀበላሉ ።
ወተሠርዎ ፡ ዘለዓለም ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚአብሔር ።(ኢሳ ፡፪፡፲ ፡፲፱ ፡)
ከእግዚአብሔር ፡ ባለሟልነት ፡ የዘለዓለም ፡ መነቀል ፡ ይመጣባቸዋል ።
ወእምስብሐተ ፡ ኃይሉ ።
በከሐሊነቱ ፡ ከሚያወርሰው ፡ ክብር ፡ የዘለዓለም ፡ መነቀል ፡ ይመጣባቸዋል ፤ መተከልን ፡ መደብ፡
እድርጎሳቸው ፡ መነቀል ፡ ይመጣባቸዋል ፡ አለ ።

፲ ፡ እመ ፡ ይመጽእ ፡ ይሴባሕ ፡ በቅዱሳኒሁ ።
በመላእክት ፡ ቃል ፡ እየተመሰገነ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ።
ወይትአኰት፡ በእለ ፡ የአምኑ ፡ ቦቱ ፡ (ቈላ ፡፫ ፡፬ ፡)
በሚያምኑት ፡ በምእመናንም ፡ ቃል ፡ እየተመሰገነ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ መነቀል ፡ ይመጣባቸዋል ።
እስመ ፡ ይትአመነነ ፡ ስምዕነ ፡ በላዕሌክሙ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ (ቈላስ ፡ ፫ ፡ ፬ ።)
ስምዕነ ፡ በላዕሌክሙ ፤ ይትአመነነ ፡ በላዕሌክሙ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡) ለናንተ ፡ የመሰከርነው ፡ ምስክ
ርነት ፡ በዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ለናንተ ፡ ይረዳልና ።

፲፩ ወበእንተዝ ፡ እጼሊ ፡ ዘልፈ ፡ በእንቲአክሙ ፡ (፩ ፡ ተሰ ፡ ፩ ፡ ፪ ።)
ስለዚህም ፡ ኹልጊዜ ፡ ስለናንተ ፡ እጸልያለሁ ።
ከመ ፡ ይከፍልክሙ ፡ ለዘጸውዐክሙ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ እናንተን ፡ የጠራለትን ፡ መንግሥቱ ፡ ሰማይን ፡ ያወርሳችሁ ፡ ዘንድ ፡ ለጠራላት፡ ለመ
ንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ያበቃችሁ ፡ ዘንድ ።
ወይፈጽም ፡ ለክሙ ፡ ኵሎ ፡ ሣህሎ ።
ይቅርታውን ።
ወሠናይቶ ።
ልጅነትን ፡ ይፈጽምላችሁ ፡ ዘንድ ። እንድም ፡ ማህሉ ፡ ልጅነትን ፡ (ወሠናይቶ ፡ ልጅነትን ፡ መደብ ፡
እድርጎ ፡ ከጽማዌ ፡ እስከ ፡ ክዊነ ፡ እሳት ፡ ያለውን ።
ወምግባረ ፡ ሃይማኖት ፡ በኃይሉ ።
ከሐሊነቱንም ፡፡ እምና ፡ የሚሠራውንም ፡ ሥራ ፡ ይፈጽምላችሁ ፡ ዘንድ ፡ እጼሊ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪ ፡ ከመ ፡ ይሰባሕ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በላዕሌክሙ ።
የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስሙ ፡ በናንተ ፡ ይመስገን ፡ ዘንድ ።
ወአንትሙሂ ፡ ቦቱ ።
እናንተም ፡ በሱ ፡ አምናችሁ ፡ ጸንታችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ።
በከመ ፡ ጸጋሁ ፡ ለአምላክነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
እንደጌታችን ፡ እንደኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቸርነት ፡ መጠን
ወአንትሙሂ ፡ ተሀልዉ ፡ ቦቱ ።
እናንተም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዳችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ (ውእቱኒ ፡ ሕልው ፡ ብክሙ ፡ ይላል ፡) እሱም
በናንት ፡ አድሮ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

<u>ክፍል ፡ ፪ ።</u>

፩ ፡ ንነግረክሙ ፡ አኃዊነ ፡ በእንተ ፡ ምጽአተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ወንድሞቻችን ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የመምጣቱን ፡ ነገር ፡ እንነግራችኋለን ፤ ገና ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ፈጥኖ ፡ እንዳይደረግ ።
፪ ፡ ወአንትሙሂ ፡ ውስተ ፡ ማኅበሩ ፡ ዑቁ ፡ ኢያደንግፁክሙ ፡ ፍጡነ ።
ባንድነቱ ፡ ያላችሁ ፡ እናንት ፡ ምጽአት ፡ ፀጳውሎስ ፡ ጊዜ ፡ ይደረጋል ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ እንዳያሸብሯችሁ ፡ ዕወቁ ።
ኢትትሐወኩ ፡ እምአእምሮ ።
ገና ፡ እንደኾነ ፡ ከማወቅ ፡ ወጥታችሁ ፡ አትናወጡ ፡ እንዳትናወጡ ፡ ዕወቁ ።
ኢበመንፈስ ።
ልብ ፡ አበላን ፡ ቢሉ ።
ወኢበነገር ።
እንደበት ፡ አሰላን ፡ ቢሉ ።
፫ ፡ ወኢበመጽሐፍ ።
መጽሐፍ ፡ ቢጽፉ ፡ እንድም ፡ (ኢበመንፈስ ፡) ምትሐት ፡ ቢያሳዩ ፡ (ኢበነገር ፡) ወሬ ፡ ቢያወሩ ፡ (ኢበመጽሐፍ ፡) መጽሐፍ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ ቢሉ ።
ከመ ፡ ዘእምኀቤነ ፡ ሰእመ ፡ ትመጽእ ፡ ዕለተ ፡ እግዚእነ ።
ጌታችን ፡ የሚመጣበት ፡ ዕለት ፡ ምጽአትን ፡ ከኛ ፡ እንዳገኙ ፡ አድርገው ፡ ምትሐት ፡ ቢያሳዩ ፡ ወሬ ቢያወሩ ፡ እንዳያሸብሯችሁ ፡ ዕወቁ ።
አልቦ ፡ ዘያስሕተክሙ ፡ ወኢበምንትኒ ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፩ ።)
በምንም ፡ በምን ፡ የሚያስታችሁ ፡ እይኑር ፡ እንዳይኖር ፡ ዕወቁ ።
ለእመ ፡ ኢቀደመ ፡ መጺአ ፡ ዘየሐውክ ፡ ወይትከሠት ።
የሚያሸብር ፡ ሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ እስቀድሞ ፡ ካልመጣ ።
ብእሴ ፡ ዓመፃ ።　　ዓመፅን ፡ የሚሠራ ።
ወልደ ፡ ሕርትምና ።
ጥፋት ፡ የሚገባው ፡ ሐሳዊ ፡ መሢሕ ፡ እስቀድሞ ፡ ካልመጣ ።
፬ ፡ ዓላዊ ።
ወንጀለኛ ።
ወሐሳዊ ፡ ዘያዐቢ ፡ ርእሶ ።
ሐሰተኛ ፡ ራሱን ፡ የሚያበልጥ ።
ወይብል ፡ ለዘሉ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምላክ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወይነብር ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወጸሐፊ ፡ ርእሶ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ፡ ፬ ፡ ፫ ።
ለቅሶ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምላክ ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ከቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገብቶ ፡ ራሱን ፡ እንደ
እግዚአብሔር ፡ የሚያደርግ ፡ (እስ ፡) እግዚአብሔር ፡ የሚሠራውን ፡ እሠራለሁ ፡ የሚል ፡ ሐሳዊ ፡ መሲሕ
እስቀድሞ ፡ ካልመጣ ፡ ዑቁ ፡ ኢያደንግፁክሙ ፡ (ሐቶታ) ከዚህ ፡ ይነብር ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስ ፤
ዮሐንስ ፡ አይገባም ፡ ይላል ፡ እንደምነው ፡ አይጣላም ፡ ቤሉ ፡ አይጣላም ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ዮሐንስ ፡ ነው
አይገባም ፤ ከዚህ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ይነብር ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለቱ ፡ ከከተማው ፡ ይግባል ፡
የካህናቱን ፡ ቤት ፡ ስቆ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከተጠራበት ፡ ብሎ ፡ ይነብር ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስ ፡
እንጂ ፡ ነገር ፡ እንደዮ ፡ ሐንስ ፡ ነው ፡ አይገባም ።

፭ ፡ ወኢትዜከሩኑ ፡ ከመ ፡ አመ ፡ ሀሎኩ ፡ ኀቤክሙ ፡ እቅደምኩ ፡ ወነገርኩክሙ ፡ ዘንተ ።
ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ በነበርሁ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሜ ፡ የጥጦስን ፡ በቅጠል ፤ የሐሳዊ ፡ መሲሕን ፡ በአበባ ፤
የምጽአትን ፡ በፍሬ ፡ መስዬ ፡ እንደነገርኳችሁ ፡ አታስቡምን

፮ ፡ ወይእዜኒ ፡ ተአምሩ ፡ ዘይክልእ ፡ እስተርእዮ ፡ እስከ ፡ ይበጽሕ ፡ ዕድሜሁ ።
አሁንም ፡ ከመታየት ፡ የከለከለው ፡ ጊዜው ፡ እስኪደርስ ፡ እንደኾነ ፡ ታውቃላችሁ ።

፯ ፡ እስመ ፡ እከየ ፡ ምክረ ፡ ኃጢአት ፡ ወድአ ፡ ይትገበር ፡ በላዕሌሁ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፭ ፡ ፴፮ ።)
የኃጢአት ፡ ተንኮል ፡ ትምህርት ፡ ፈጽሞ ፡ በሱ ፡ ይደረጋልና ፡ የሚደረግበት ፡ ጊዜው ፡ እስኪደርስ ፡
እንደኾነ ፡ ታውቃላችሁ ። ዝምክሮሙ ፡ ወዝግብሮሙ ፡ የኃልፍ ፡ ወይሠዐር ፡ እንዲል ፡ (ግብ፡ ሐዋ ፤
፭ ፡ ፴፰ ።)
ወዳዕሙ ፡ ይእዜሰ ፡ እኍዝ ፡ እስከ ፡ ይትኃደግ ፡ እማእከል ።
ከማእከለ ፡ ሠራዊት ፡ ተለይቶ ፡ በመንግሥት ። እንድም ፤ (በማእከል ፡) በማእከለ ፡ ሠራዊት ፤ በመን
ግሥት ፡ እስኪጣል ፡ ድረስ ፡ ተገቷል ፡ እንጂ ፡ ወድአ ፡ ይትገበር ። (አንድም ፡ መልስ ።)
እስመ ፡ እከየ ፡ ምክረ ፡ ኃጢአተ ፡ ወድአ ፡ ይትገበር ፡ በላዕሌሁ ።
(እስመ ፡ እከየ ፡ ምክረ ፡ ኃጢአት ፡ ወድአ ፡ ይትገበር ፡ በላዕሌሁ ፡ እስከ ፡ ይትኀደግ ፡ እማእከል ፡
ብለህ ፡ አቅና ። )
ከማእከለ ፡ ሠራዊት ፡ ተለይቶ ፡ በገሃነም ፡ (በማእከል ፡( በማእከለ ፡ ሠራዊት ፡ በገሃነም ፡ እስኪጣል ፡
ድረስ ፡ የኃጢአት ፡ ተንኮል ፡ ትምህርት ፡ በሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ይደረጋልና ፡ ከመታየት ፡ የከለከለው ፡ ጊዜው ፡
እስኪደርስ ፡ እንደኾነ ፡ ታውቃላችሁ ።
ወዳዕሙ ፡ ይእዜሰ ፡ እኍዝ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ ተገኝቷል ።

፰ ፡ ወይእተ ፡ አሚረ ፡ ይትከሠት ፡ ወልደ ፡ ዓመፃ ።
ያንጊዜ ፡ በዓመፃ ፡ የተወለደ ፡ ሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ ይገለጻል ።
ኃጥእ ።
ኃጢአተኛ ።
ዘሀለዎ ፡ ያጥፍኦ ፡ መንፈሱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሕይወቱ ፡ መንፈሱ ፡ ቅዱስ ፡ ያጠፋው ፡ ዘንድ ፡ ያለው ። (ሐተታ) ፡ ዮሐንስ ፡
በረቂቅ ፡ የእሳት ፡ ጦር ፡ ወግቶ ፡ ሲጥለው ፡ እይቋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።
ወይሥዕሮ ፡ በእስተርእዮተ ፡ ምጽአቱ ። (ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፬ ። ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፲፭ ፡ ፳ ።
መጥቶ ፡ በተገለጸ ፡ ጊዜ ፡ ያጠፋዋል ።

፱ ፡ ወምጽአቱሰ ፡ ለዝንቱ ፡ በኃይሉ ፡ ለሰይጣን ።
የዚህ ፡ የሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ አመጣጡ ፡ ሰይጣን ፡ የምትሐት ፡ ተአምራት ፡ እያደረገለት ፡ ነው ።
በኵሉ ፡ ኃይል ።
ምውት ፡ በማንሣት ።
ወትእምርት ።
ድውይ ፡ በመፈወስ ።
ወመንከር ፡ በሐሰት ። (ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፳፬ ።)
ጋኔን ፡ በማውጣት ።

www.ethiopianorthodox.org

፲ ፡ ወበኵሉ ፡ አስሕቶ ፡ ዘኃጢአት ፡ ለሕርቱማን ። (፪ቆሮ ፡ ፲፪፡ ፲፪ ፡ ፫ ።)
ሕርቱማንን፡በማሳት ፡ ያምትሐት ፡ ተአምራት ፡ እያደረገለት ፡ ነው ፡ (ዘኃጢአት ፡ አስ ፡) አስሐቶ ፡ ዝ ፡ ጳውሎስ ፡ ካለው ፡ ሲለይ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲ ፡ ፮ ።)
እስመ ፡ ኢተወክፉ ፡ ፍቅረ ፡ ቃለ ፡ ጽድቅ ፡ በዘየሐይዉ ።
በሚያምኑ ፡ በሚድኑ ፡ ገንዘብ ፡ ወዶ ፡ በሠራት ፡ በወንጌል ፡ ፀቁኬ ፡ ኢያስሕቶክሙ ፡ ያለውን ፡ አልተቀበሉምና ።
፲፩ ፡ ወበእንተዝ ፡ ይፌኑ ፡ ሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይለ ፡ መስሕት ። (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳፬ ፡)
(ስለዚህ ፡ (ኃይለ ፡ መስሕት ፡) የምትሐት ፡ ተአምራት ፡ ያዝዝባቸዋል ፡ ኃይለ ፡ መስሕት ፡ ዲያብሎስ ፡ የሚያመጣውን ፡ የምትሐት ፡ ተአምራት ፡ ያዝዝባቸዋል ።
ከመ ፡ ይእመኑ ፡ በሐሰት ።
በሐሰተኛው ፡ መሢሕ ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ።

፲፪ ፡ ከመ ፡ ይትኰነኑ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ኢየአምኑ ፡ በጽድቅ ። (ሔዝ ፡ ፳ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭ ።)
በውነተኛው ፡ መሢሕ ፡ የማያምኑት ፡ ኹሉ ፡ ይፈረድባቸው ፡ ዘንድ ።
ወየኀብሩ ፡ በዓመፃ ።
በክህደት ፡ አንድ ፡ የሚኾኑት ፡ ኹሉ ፡ ይፈረድባቸው ፡ ዘንድ ።

፲፫ ፡ ወንሕነሰ ፡ አኃዊነ ፡ ርቱዕ ፡ ናእኵቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘልፈ ፡ በእንቲአክሙ ፡ እለ ፡ አፍቀረክሙ እግዚአብሔር ። (ም ፡ ፩ ፡ ፫ ፡ ፬ ።)
ወንድሞቻችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለወደዳችሁ ፡ ስለናንት ፡ ግን ፡ ሁልጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እኛ ፡ ልናመሰግነው ፡ ይገባል ።
እስመ ፡ ኀረየክሙ ፡ ወተሣሃለክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርእሰ ፡ ሕይወት ፡ ወተቀድሶ ፡ መንፈስ ፡ ወበሃይማኖተ ፡ ጽድቅ ። (ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፬ ።)
የሕይወት ፡ መገኛ ፡ የልጅነት ፡ ባለቤት ፡ እግዘ አብሔር ፡ (ኀረየክሙ ፡ ወተሣሃለክሙ ፡ በሃይማኖተ ጽድቅ ፡) በሃይማኖት ፡ መርጧችኋል ፡ ይቅር ፡ ብሏችኋልና ። አንድም ፡ የሕይወት ፡ ባለቤት ፡ የሕይወት መገኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ኀረየክሙ ፡ በሃይማኖት ፡ ተሣሃለክሙ ፡ በተቀድሶ ፡ መንፈስ ፡) በሃይማኖት ፡ መርጧችኋል ፡ በልጅነት ፡ ይቅር ፡ ብሏችኋልና ።

፲፬ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ ጸውዐክሙ ፡ በትምህርተ ፡ ወንጌሉ ።
በወንጌል ፡ ትምህርት ፡ እናንተን ፡ በጠራበት ፡ በሃይማኖት ፡ መርጧችኋልና ።

ከመ ፡ ትሕየዉ ፡ በስብሐቲሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጌትነቱን ፡ ወርሳችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ (ክብሩንም ፡ ብትል ፡) አንድም ፡ (ከመ ፡ ትሕየዉ ፡ በስብሐቲሁ ። ዘበእንቲአሁ ፡ ጸውዐክሙ ፡) በወንጌል ፡ ትምህርት ፡ እናንተን፡ የጠራለትን ፡ ክብሩን ፡ ጌትነቱን ፡ ወርሳችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ መርጧችኋልና ።

፲፭ ፡ ወይእዜኒ ፡ እኃዊነ ፡ ቁሙ ።
አሁንም ፡ ወንድሞቻችን ፡ ጽኑ ።
ወዕቀቡ ፡ ትእዛዘ ፡ ዘመሀሩክሙ ፡ ወሠርዑክሙ ፡ ዘበቃልነ ።
ከቃላችን ፡ እግኝተው ፡ ያስተማሯችሁን ፡ ትምህርት ።
ወዘበመጽሐፍነ ። (ም ፡ ፫ ፡ ፮) ።
ከመጽሐፋችን ፡ እግኝተው ፡ የሠሩላችሁን ፡ ሥርዓት ፡ ጠብቁ ። አንድም ፡ ዘበቃሎሙ ፡ ወዘበመጽሐፎሙ ፡ ይላል ፡ ከቃላችን ፡ እግኝተው ፡ በቃላቸው ፡ ያስተማሯችሁን ፡ ትምህርት፤ ከመጽሐፋችን ፡ እግኝተው ፡ በመጽሐፋቸው ፡ የሠሩላችሁን ፡ ሥርዓት ፡ ጠብቁ ።

፲፮ ፡ ወውእቱ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
እሱ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ወእግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ዘአፍቀረነ ።
የወደደን ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ።
ወወሀበነ ፡ ፍሥሓ ፡ ዘለዓለም ።
ልጅነትን ፡ የሰጠን ።

www.ethiopianorthodox.org

ወተስፋ ፡ ሠናየ ።

በጎውን ፡ ሃይማኖት ፡ የሰጠኝ ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ።

፲፯ ፡ ጸጋሁ ፡ ውእቱ ፡ ያስተፍሥሕክሙ ፡ ልበክሙ ።

ጸጋውን ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ ያሰኛችሁ ። አንድም ፡ (በጸጋሁ ፡) በጸጋው ፡ ደስ ፡ ያሰኛችሁ ። አንድም ፡ (ጸጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡) የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የጌታችን የኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ጸጋው ፡ ደስ ፡ ያሰኛችሁ ።

ወያጽንዕክሙ ፡ በኵሉ ፡ ምግባር ፡ ወበኵሉ ፡ ቃል ፡ ሠናይ ። (፩ ፡ ተሰ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ፡)

በበጎው ፡ ሥራ ፡ በበጎው ፡ አነጋገር ፡ እንድትጸኑ ፡ ያድርጋችሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

፩ ፡ ወይእዜኒ ፡ አኃዊነ ፡ ጸልዩ ፡ ለነ ፡ (ቈላ ፡ ፬ ፡ ፫ ።)

አሁንም ፡ ወንድሞቻችን ፡ ጸልዩልን ።

ከመ ፡ ይሩጽ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይሰባሕ ፡ በከመ ፡ በኀቤክሙ ።

ወንጌል ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ እንደተገለጠ ፡ ከኹሉ ፡ ደርሶ ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ጸልዩ ።

፪ ፡ ወከመ ፡ ንድኃን ፡ እምሰብእ ፡ እኩያን ፡ ወዓላውያን ።

ከክፉ ፡ ሰዎች ፡ ከዓላውያን ፡ እጅ ፡ እንድንን ፡ ዘንድ ።

እስመ ፡ አኮ ፡ ኵሉ ፡ ዘየአምን ።

ኹሉ ፡ የሚያምን ፡ አይደለምና ፡ ንድኅን ፡ እምሰብእ ፡ እኩያን ፡ አንድም ፡ ኹሉ ፡ ያመነ ፡ አይደለ ምና ፡ ይሩጽ ፡ ወይሰባሕ ።

፫ ፡ ወእግዚአብሔርሰ ፡ ማእምን ፡ ወጻድቅ ፡ ዘያጸንዓክሙ ፡ ወየዐቅበክሙ ፡ እምኵሉ ፡ እኩይ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፱ና ፡ ፲ ፡ ፲፫ ። )

በሃይማኖት ፡ የሚያጸናችሁ ፡ ከክፉ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ የሚጠብቃችሁ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የታመነ ቸር ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ።

፬ ፡ ንትአመነክሙ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ትገብሩ ፡ ዘአዘዝናክሙ ፡ (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፯ ። ገላትያ ፡ ፭፡፲ ዘአዘዝናክሙ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትገብሩ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታዝዘን፡ እግዚአብሔር ፡ አዝዟችኋል ፡ ብለን ፡ ያዘዝናችሁን ፡ ትእዛዝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነት ፡ ትፈጽሙት ዘንድ ፡ እንማልዳችኋለን ።

ወገበርክሙኒ ።

እንደገና ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ ከዚህም ፡ ቀደም ፡ ሠርታችሁታል ።

፭ ፡ ወእግዚእነ ፡ ያርትዕ ፡ ልበክሙ ፡ ውስተ ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወውስተ ፡ ተስፋሁ ፡ ለክርስቶስ ።

ጌታችን ፡ ልቡናችሁን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደመውደድ ፡ በክርስቶስ ፡ ወደሚገኝ ፡ እለኝታ ፡ ያቅናው

## ክፍል ፡ ፬ ።

፮ ፡ አኃዊነ ፡ ንኤዝዘክሙ ፡ በስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ወንድሞቻችን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አዝዟችኋል ፡ ብለን ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ታዝዘን ፤ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ኾነን ፡ እናዝዛችኋለን ።

ተገኀሥዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ቢጽ ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ በትምይንት ፡ ወአኮ ፡ በሥርዐት ፡ ዘሠራዕናሆሙ ፡ ማቴ ፡ (፲፰ ፡ ፲፯ ፡ ሮሜ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ። ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲ ።)

እኛ ፡ በሠራንላችሁ ፡ ሥርዓት ፡ ያይደለ ፡ በተንኮል ፡ አነዋወር ፡ የሚኖሩ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያንን ፡ ተለ ያዩዋቸው ፡ ብለን ፡ እናዝዛችኋለን

www.ethiopianorthodox.org

፯ ፡ ለሊከሙ ፡ ተአምሩ ፡ ከመ ፡ ርቱዕ ፡ ትትመሰሉነ ።
እኛን ፡ ትመስሉ ፡ ዘንድ ፡ እንዲገባ ፡ እናንተ ፡ ቅሉ ፡ ታውቃላችሁ ።
ከመ ፡ ኢሰላዕነ ፡ ላዕሌክሙ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፯ ፡ ፩ ፡ ተሰ ፡ ፩ ፡ ፯ ።)
ለክብራችሁ ፡ እንዳልላላን ።
፰ ፡ ወኢበላዕነ ፡ እክለ ፡ ባዕድ ፡ በከንቱ ።
አስተምረናል ፡ ብለን ፡ ሳንጽር፡ ሳንግር ፡ ከብዙዎችሁን ፡ እንዳልተመገብን ።
ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ዘንጻሙ ፡ ወንውርሕ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ወንትጌበር ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ።)
በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ ይዘን ፡ ሌት ፡ ከስፌት ፡ ቀን ፡ በትምህርት ፡ ደክመን ፡ እንመ
ገባለን ፡ እንጂ ።
ከመ ፡ ኢናክብድ ፡ ላዕሌክሙ ።
እናንተን ፡ እንዳናስቸግር ፡ በናንተ ፡ ሥርዓት ፡ እንዳናጸና ።
፱ ፡ ወአኮሰ ፡ ዘኢኮነ ፡ ብውሑነ ፡ (ማቴ ፡ ፲ ፡ ፲ ።)
እንዲሁም ፡ ማለታችን ፡ አስተምሮ ፡ ዋጋ ፡ መብላት ፡ የማይገባን ፡ ኾኖ ፡ አይደለም ።
ዳዕሙ ፡ አርአያ ፡ ከመ ፡ ንኩንከሙ ፡ ከመ ፡ አንትሙ ፡ ትትመሰሉነ ፡(፩ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፯ ።)
እኛን ፡ እንድትመስሉን ፡ አብነት ፡ እንኾናችሁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
፲ ፡ ወአመሂ ፡ ሀለውኩ ፡ ኀቤክሙ ፡ ዘንተ ፡ አዘዝኩክሙ ።
ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ በነበርሁ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ነግሬያችኋለሁ ።
ዘኢይፈቅድ ፡ ይትቀነይ ፡ ኢይሴሰይ ፡(ዘፍጥ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ።)
መስከ ፡ አሽ ፡ አይመገብ ፡ ብዬ ።
፲፩ ፡ ሰማዕነ ፡ ከመቦ ፡ እምውስቴትክሙ ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ በሁከት ።
ምን ፡ ሰምተሀብናል ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ ከናንተ ፡ ወገን ፡ በሁከት ፡ አናዋር ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ እን
ዳሉ ፡ ሰምተናል ፤ መለክ ፡ ሲያሹ ፡ ውሎ ፡ ከሰው ፡
ሰደቃ ፡ መሠራትን ፡ ሁከት ፡ እላት ።
ወአልቦ ፡ ዘይትቀነዩ ፡
ተግባረ ፡ እድ ፡ የማይዙ ፡ ከናንት ፡ ዘንድ ፡ እንዳሉ ፡ ሰምተናል ።
ዓዲ ፡ መስተሐውራን ።
በዚያም ፡ ላይ ፡ ነገር ፡ አዋላጆች ፡ ናቸው ፤ ሥራ ፡ ከፈቱ ፡ ይህ ፡ ይቀለልን ።
፲፪ ፡ ወእለ ፡ ከመዝ ፡ ንኤዝዞሙ ፡ ወንጌሥጾሙ ፡ በስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያሉትን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አዝዟችኋል ፡ ብለን ፡ በጌታችን ፡ በኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እንመክራቸዋለን ፡ እናስተምራቸዋለን ።
ከመ ፡ በየውሃት ፡ ወበጽምው ፡ ይትገበሩ ፡ ተግባሮሙ ፡ ወይሴሰዩ ፡ ሲሳዮሙ ፡ (፩ ፡ ተሰ ፡ ፬ ፡ ፲፩ ።)
በጸጥታ ፡ በዝግታ ፡ በቅንነት ፡ ኾነው ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ ይዘው ፡ ይመገቡ ፡ ዘንድ ።
፲፫ ፡ ወአንትሙሂ ፡ አኀዊነ ፡ ኢትትሀከዩ ፡ ገቢረ ፡ ሠናይ ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ፡ (ገላት ፡ ፮ ፡ ፱ ።)
አሁንም ፡ ወንድሞቻችን ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖት ፡ ከመሥራት ፡ ቸል ፡ አትበሉ ።
፲፬ ፡ ወእመቦ ፡ ዘኢይትኤዘዝ ፡ ለቃልክሙ ፡ ወለመጽሐፍክሙ ፡ ይትፈለጥ ። (ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፯ ። ፩ ፡ ፩ቆሮ
፭ ፡ ፱ ፡ ፲፩ ።)
በቃላችሁ ፡ ላስተማራችሁት ፡ ትምህርት ፡ በመጽሐፋችሁ ፡ ለሠራችሁት ፡ ሥራት ፡ የማይታዘዝ ፡
ቢኖር ፡ አንድም ፡ ለቃልነ ፡ ወለመጽሐፍነ ፡ ይላል ፤ ከቃላችን ፡ አግኝታችሁ ፡ በቃላችሁ ፡ ለአስተማራ
ችሁት ፡ ትምህርት ፡ በመጽሐፋችሁ ፡ ለሠራችሁት ፡ ሥርዓት ፡ የማይታዘዝ ፡ ቢኖር ፡ ይለይ ።
ወኢትትሀወልዎ ፡ አትገናኙት ።
ከመ ፡ ይትኀፈር ፡ ይገሠጽ ፡ ዘንድ ።
፲፭ ፡ ወከመሰ ፡ ጸላዒ ፡ ኢትረስይዎ ፡ እንደባዕድ ፡ ግን ፡ አታድርጉት ።
አላ ፡ ገሥጽዎ ፡ ከመ ፡ እኁክሙ ፡ (ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፭ ።)

www.ethiopianorthodox.org

ወንድሞቻችሁ ፡ እንደመኙት ፡ ወንድሞቻችሁን ፡ እንድትመስሉ ፡ እንድትገሥጹ ፡ ምክሩን ፡ ትእዛዙ
ሩት ፡ አንድ ፡ ።

፲፩ ፡ ወወሀቦሙ ፡ ለቃላቲሁ ፡ ወለዝ ፡ የፅፍኩ ፡ በአዝ ፡
የፍቅር ፡ የአንድነት ፡ ሠላምታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሁሉ ፡ እንደሚሰጥ ፡ ይስጣችሁ ፡
ወሰላሙ ፡ ትባርክ ፡ ። ... ሰላምታ ፡ ከሁሉ ፡ ጋር ፡ ይስጣችሁ ፡ ።
ወእግዚእን ፡ የሁሉ ፡ ምክሩ ፡ ዘአክሎ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፮ ፡ ፩ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፳ ፡)
ጌታችን ፡ ከሁላችሁ ፡ ጋራ ፡ አይርቃችሁ ፡ ይኑር ፡

፲፪ ፡ ዘንተ ፡ አምኃ ፡ እሐፍክ ፡ ለክሙ ፡ በእደዊየ ፡ አነ ፡ ጳውሎስ ፡ (፩ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፳፩ ፡)
ይህን ፡ ከታብ ፡ እኔ ፡ ጳውሎስ ፡ በእጄ ፡ ጻፍኩላችሁ ፡ (ሐዋ ፡ ፫) እንዳለፈው ፡
ወዘንቱ ፡ ትእምርትየ ፡ ውስተ ፡ ኩሉ ፡ መጻሕፍትየ ፡
በምጽፈው ፡ ከታብ ፡ ኹሉ ፡ ምልክቴ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ።

፲፫ ፡ ከሙዝ ፡ እጽሕፍ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሁሉ ፡ ምክሩ ፡ ዘአክሎ ፡ (፪ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ፡
እንዲህ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እያልሁ ፡ እጽፋለሁና ፡ ጸጋ ፡ ጸጋ ፡ ያለበት ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ተቀበሉት
የሌለበት ፡ የኔ ፡ አይደለም ፡ አትቀበሉት ፡ ለማለት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ።

አሜን ፤ በውነት ፡ ።

ተፈጸመት ፡ ጦማር ፡ መልእክቱ ፡ ኀበ ፡ ሰብእ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ወተጽሕፈት ፡ በሉዶቅያ ፡ ወተፈነወት ፡ በእደ
ጢቆስ ፡ ።
በሉዶቅያ ፡ የተጻፈች ፡ በጢኪቆስ ፡ እጅ ፡ ለተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ፡ የተላከች ፡ ሁለተኛ ፡ መልእክት ፡ ደረ
ሰች ፡ ተፈጸመች ፡ ።

ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ።

አነሣሥቶ ፡ ሳስጀመረን ፡ አስጀምሮ ፡ ሳስጨረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፡ ።

ethiopianorthodox.org